September 2021, Amharisk

# የኮሮና ቫይረስ ክትባት

## – (ሞደርና)

### ይህን ክትባት ለመከተብ እድል ላገኘ ሰው መረጃ

አዲሱ የኮሮና ቫይረስ የመተንፈሻ አካልን የሚጎዳ በሽታ ነው። በርካታ ሰዎች ቀለል ያሉትን ወይም ጠቅላላ ምልክቶች የማይታይባቸው ሲሆኑ፣ ነገር ግን አንዳንዶች በጽኑ ይታመማሉ። አረጋዊያን እና ቀድሞውኑ አንዳንድ ሌሎች በሽታዎች ያለባቸው ሰዎች በዚህ በሽታ የመጠቃት ወይም የመሞት ከፍተኛ እድል አላቸው፡ ፡ የኮሮና ቫይረስ ክትባት የኮቪድ-19 በሽታን ይከላከላል። ዋና ግቡ ህይወትን እና ጤናን መጠበቅ ነው።

### ይህን የኮሮና ቫይረስ ክትባት ማን መውስድ ይችላል?

በብሔራዊ የክትባት መርሃ ግብር በኩል የሚሰጠው የኮሮና ክትባት በኖርዌይ ውስጥ ለሚቆዩ ሰዎች ይሰጣል። ክትባቱ በነጻ የሚሰጥ እና በፈቃደኝነት ላይ ተመስርቶ የሚወሰድ ነው።

### ክትባቱን እንዴት ማግኘት እችላለሁ?

ክትባቱ የሚሰጠው ለማን እንደሆነ፣ ክትባቱ እንዴት እንደተቀናጀ እና መቼ እንደሚፈጸም የበለጠ መረጃ ለማግኘት የኮሚዩናዎን ድረ ገጽ ይመልከቱ።

### ክትባቱ የሚከናወነው በዚህ መንገድ ነው

ክትባቱ በላይኛው ክንድ ላይ በመወጋት የሚሰጥ ነው። ክትባቱን ከመውሰድዎ በፊት ጤነኝነት የሚሰማዎ ስለመሆንዎት የሚጠየቁ ሲሆን እንዲሁም ከዚህ በፊት ክትባቶችን ወስደው ስላሳዩት የሰውነትዎ ምላሽ እንዲገልጹ ይጠየቃሉ። ከዚህ በፊት በኮሮና ቫይረስ በሽታ ተይዘው ከነበረ ወይም የኮሮና ቫይረስ ክትባት ከዚህ በፊት ከወሰዱ፣ እርጉዝ ከሆኑ፣ ምንም አይነት ከመድኃኒት ጋር የሚገናኝ የሰውነት መቆጣት/አለርጂት ካለብዎ፣ መድኃኒቶችን የሚጠቀሙ ከሆነ ወይም ሌላ የጤና ችግር ካለብዎ ማሳወቅዎን ያስታውሱ። ለቡድንዎ የሚተገበረውን የክትባት መጠን እና የተቀመጠውን የጊዜ ሰሌዳ መመሪያን ይከተሉ። ይህ በክትባት ቦታ የሚሰሩትን ሰዎች ይረዳል። በተወሰነው ጊዜ የክትባቱን መጠን መውሰድ አስፈላጊ ነው። በከፍተኛ ደረጃ ህመም ካጋጠምዎ ወይም ሙቀትዎ ከ38 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ በላይ ከሆነ ክትባቱን ማቆየት የተለመደ ነው። ክትባቱን ከተከተቡ በኋላ ለ20 ደቂቃዎች በክትባቱ ቦታ እንዲጠብቁ ይጠየቃሉ።

### ይህ ክትባት እንዴት ይሰራል?

ክትባቱ በኮሮና ቫይረስ ላይ ያሉትን ድንገጫዎች(መሸፈኛዎች)መልዕክተኛ(ሜሴንጀር አርኤንኤን)የያዘ ነው። ሰውነታችን እነዚህን መሸፈኛዎችን ጎጂ ባልሆነ መልክ ኣባዝቶ በሽታ የመከላልን አቅም በነሱላይ እንዲለማመድ ያደርገዋል። በዚህ መንገድ ሰውነታችን የኮሮና ቫይረሱን በማወቅ እና እንዲሁም ቫይረሱ የሚጎዳ እንዳይሆን መከላከል እንዲችል ያደርጋል። በክትባቱ ውስጥ የተላከው መልእክተኛው አርኤንኤ በጂን ላይ ምንም አይነት ተጽዕኖ ሳያሳድር በአካላችን ውስጥ በፍጥነት ይከፈላል።

ክትባቱ ህይወት ያለው ቫይረሶችን አልያዘም ስለዚህም የኮሮና በሽታን አያሲዝም። የኮሮና ቫይረስ ክትባት በሽታን ለመከላከል የሚሰራ ነው። በሰውነት ውስጥ ያለውን የኮሮና በሽታን ግን ማዳን አይችልም።

ከዚህ በፊት ይህን ክትባት ለመስራት የተጠቀሙት ዘዴ ለበሽታዎች ማዳኛ አገልግሎት ላይ ውሎ አያውቅም። ነገር ግን ቴክኖሎጂው ይታወቃል። እንዲሁም በካንሰር በሽታ ህክምና ላይ ለአገልግሎት ውሏል።

FHI

## ክትባቱ ምን ያህል ይሠራል?

ክትባቱ አዲሱ የኮሮና ቫይረስ ከሚያስከትለው በሽታ ይከላከላል። አንደኛውም ሆነ ሁለተኛው የክትባት መጠን ከተወሰደ በኋላ ከከባድ በሽታ የመከላከል አቅሙ ከፍተኛ ነው። በኮሮና ቫይረስ እንዳይያዙ ጥሩ መከላከያ ለማግኘት ሁለት የክትባት መጠን መውሰድ ያስፈልጋል። ጥበቃው ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቆይ ገና አናውቅም። ጥበቃው በጊዜ ሂደት እየቀነሰ ከመጣ የሚያድሱ የክትባት መጠኖችን መውሰድ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። ክትባቶቹ ተጨማሪ ስርጭትን ሙሉ በሙሉ አይከላከልም። ስለዚህም አሁን ያለው የበሽታው መቆጣጠሪያ ምክር መከተልን መቀጠሉ ጠቃሚ ነው።

## የጎንዮሽ ጉዳቶች

አብዛኞቹ የጎንዮሽ ጉዳቶች ክትባቱን ከተከተቡ በኋላ ባሉት የመጀመሪያዎቹ ቀናት ውስጥ ይከሰታሉ። የኮሮና ክትባት በሌሎች ክትባት ላይ ከተለመዱት የጎንዮሽ ጉዳቶች የበለጠ የጎንዮሽ ምልክቶችን ያስከትላል። ምልክቶቹ ብዙውን ጊዜ መለስተኛ እስከ መካከለኛ ናቸው እንዲሁም ከጥቂት ቀናት በኋላ ይጠፋሉ ነገር ግን አንዳንዶች የበለጠ ከባድ ምልክቶች ይኖራቸዋል። ወጣት ሰዎች ብዙውን ጊዜ በዕድሜ ከገፉ ሰዎች በመጠኑ የከፋ የጎንዮሽ ጉዳት ያጋጥማቸዋል።

አብዛኞቹ የተከተቡት ሰዎች መድሀኒቱን በተወጉበት ቦታ ላይ ህመም ይሰማቸዋል። ሌሎች የተለመዱ የጐንዮሽ ጉዳቶች ድካም፣ የራስ ምታት፣ የጡንቻ ህመሞች፣ ብርድ ብርድ ማለት፣ የመገጣጠሚያ ህመሞች ፣ ማቅለሽለሽ/ማስታወክ ፣ ያበጠ እና የህመም ስሜት በብብት ላይ ባለ የሊምፍ ሻርትል  እና ትኩሳትን ይጨምራሉ። እነዚህ የጐንዮሽ ጉዳቶች ሁለተኛውን የመድሀኒት መጠን ከወሰዱ በኋላ የሚታዩ ናቸው።

ከባድ የጎንዮሽ ጉዳቶች ያልተለመዱ ናቸው። ያልተለመዱ የጎንዮሽ ጉዳቶች የጡንቻ መቆጣት (ምዮቻርዲቲስ) እና ፐሪቻርዲቲስ ያካትታሉ። ብዙውን ጊዜ የሚከሰተው ከሁለተኛው የክትባት መጠን በኋላ እና  በጉርምስና ዕድሜ ላሉ እና በወጣቶች ላይ ነው። እንደ ከባድ የአለርጂ ምላሽ እና የልብ እብጠት ያሉ ያልተለመዱ የጎንዮሽ ጉዳቶች ከተከሰቱ ሊታከሙ ይችላሉ። እስካሁን ያልታወቁ ያልተለመዱ የጎንዮሽ ጉዳቶችን ፣ ወይም ክትባትን ከተከተቡ ከጊዜያት በኋላ ብቻ የሚታዩ የጎንዮሽ ጉዳቶችን አይከሰቱም ማለት አንችልም።

## የጐንዮሽ ጉዳቶችን ካየሁ ምን ማድረግ አለብኝ ?

ያልተጠበቁ፣ ከባድ ወይም ለረዥም ጊዜ የቆዩ ምልክቶች ካጋጠምዎት ለህክምና ወይም ለምክር ሀኪምዎን ወይም ሌላ የጠና አጠባበቅ ሰራተኛን ያነጋግሩ። ይህ በክትባቱ ምክንያት ነው ብለው ቢያስቡም እንዲሁም ባይሆንም ተፈጻሚ ይሆናል። የጤና አጠባበቅ ሰራተኞች በክትባት ምክንያት የመጣ ነው ብለው የሚጠረጥሯቸውን ማናቸውም ከባድ ወይም ያልተጠበቁ ምላሾችን ሪፖርት የማድረግ ግዴታ አለባቸው፡ ፡ ራስዎትም በ helsenorge.no. በኩል ማስታወቂያ መላክ ይችላሉ።

## ተጨማሪ ማረጋገጫ

ይህ የኮረና ቫይረስ ክትባት በትላልቅ ጥናቶች ሲመረመር የቆየ ሲሆን በዚህም ብዙ ሺህ ሰዎች ክትባቱን ወስደዋል። ጥናቶቹ እንደሌሎች ክትባቶች በተመሳሳይ መንገድ ሲከናወኑ የቆዩ ሲሆን ነገር ግን የምልከታው ጊዜው አጭር ነው። የመድሀኒት ተቆጣጣሪ ባለስልጣናት ለክትባቱ በሁኔታ ላይ የተመሰረተ ማረጋገጫ ሰጥተዋል። ይህም ማለት ክትባቱ የሚሰጠው ጥቅም ከስጋቱ አንፃር ምን ያህል እንደሆነ በቂ መረጃ ማግኘት ይቻላል ማለት ነው። ነገር ግን የክትባት አምራቹ ጥናቶችን መቀጠል እና ለመድሀኒት ተቆጣጠሪው ባለስልጣናቱ የተገኘውን መረጃ በቀጣይነት ማቅረብ ይጠበቅበታል።

## እኔ የወሰድኩት ክትባት የትኛው ነው?

የኮረና ቫይረስ ክትባት ከተሰጥዎት በኑሮዊጂያን የበሽታ መከላከያ መዝገብ፣ SYSVAK ውስጥ ይመዘገባል፡ ፡ መረጃውን በ helsenorge.no. ላይ ማግኘት ይችላሉ።

## የበለጠ ማወቅ ይፈልጋሉ?

እባክዎ ሀኪምዎን ወይም ሌላ የጤና አጠባበቅ ሰራተኛ ይጠይቁ ወይም የኖርዌጂያን የጤና ተቋም ድረገጽ የሆነውን ይመልከቱ: https://www.fhi.no/kvp

FHI